**በ2015 ዓ.ም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መግቢያ ፈተና ወስዳችሁ የማለፊያ ነጥብ**

**ላመጣችሁ ተማሪዎች በሙሉ**

የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ በተፈጥሮ ሳይንስና በምህንድስና ልዩ ተሰጥኦና ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች አወዳድሮ በመቀበል ማስተማር ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም በ2015 ዓ.ም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መግቢያ ፈተና ወስዳችሁ በተፈጥሮ ሳይንስ ትምህርት ዘርፍ የማለፊያ ነጥብ ያስመዘገባችሁ ተማሪዎች የትምህርት ሚኒስቴር ባወጣው መስፈርትና ቀናት እንድትመዘገቡ እናበረታታችኋለን፡፡

አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲን ምረጡ! **ልዩ ከሚያደርጉን ነገሮች መካከል፡-**

1. ለአዲስ ገቢ ተማሪዎች ልዩ ትኩረት የሰጠ ምቹና ቀልጣፋ አገልግሎት እንሰጣለን፡፡
2. በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ አሉ የተባለ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ሙሁራንን ቀጥረን እናሰራለን፡፡
3. በሀገራችን የመጀመሪያ በሆነ የጊዜው ቴክኖሎጂ የተሟላ ስቱዲዮ ዘመናዊ በመጠቀም ከክፍል ውስጥ ትምህርት በተጨማሪ በኤልክትሮኒክ (ኢ-ለርኒንግ) ትምህርት የተማሪዎቻችንን እውቀትና ክህሎት እናጎለብታለን፡፡
4. የመማር ማስተማር ስርዓታችን ተማሪዎች የራሳቸውን ስርዓተ ትምህርት (curriculum) እንዲቀርጹ ዕድል የሚሰጥና ዓለም አቀፍ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲዎችን ልምድ በመቀመር የተዘጋጀ ነው፡፡
5. በትምህርታቸው ልዩ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎችን ልዩ ፈተና በመስጠት በአጭር ጊዜ ወደሚቀጥለው ሴሚስተር ትምህርት በማሳለፍ ከታቀደው ዓመት ባነሰ ጊዜ (Fast Track) ባለድግሪ እናደርጋለን፡፡
6. ከፍተኛ ነጥብ የሚያስመዘግቡ ተማሪዎችን ተጨማሪ ኮርሶች እንዲወስዱ በመፍቀድ በአንድ ጊዜ ከአንድ ድግሪ በላይ (Dual Degree) እንዲያገኙ እናደርጋለን፡፡
7. በከፍተኛ ውጤት ለሚመረቁ ተማሪዎች በቀጥታ የሁለተኛ ዲግሪ ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ ስኮላርሺፕ እንሰጣለን፡፡
8. የICT ማዕከላትና ፈጣን የብሮድ ባንድ ኢንተርኔት አገልግሎቶችን ጨምሮ ጥራታቸውን የጠበቁ የተሟሉ የትምህርት መሰረተ ልማቶች አሉን፡፡
9. በተሟሉ ምቹ ቤተ-መፀሀፍት በሳምንት ለ ቀናት የ24 ሰዓት አገልግሎት እንሰጣለን፡፡
10. ለሴት ተማሪዎች የተለየ የተሟላ ቤተመጽሐፍት አለን፡፡

11.በትምህርታቸው የላቀ ውጤት የሚያመጡ ተማሪዎችን የሚያበረታታ ልዩ ስርዓት አለን።
12.ለተማሪዎቻችን የአጭርና የረጅም ጊዜ የተግባር ስልጠና ዕድል መፍጠር የሚያስችል በርካታ የሀገር ውስጥና ውጭ ሀገራት ተቋማትና ኢንዱስትሪዎች ጋር ጠንካራ ግንኙነት አለን።
13.ጥናትና ምርምር ተኮር ትምህርት ለመስጠትና ቴክኖሎጂን መቅዳት፤ ማላመድና መፍጠር የሚያስችሉ በሀገር አቀፍ ደረጃ እውቅና ያላቸው ስምንት የልህቀት ማዕከላት አሉን።
14.አረንጓዴና ነፋሻ የሆነ ለመማር፤ ለማጥናትና ለመኖር የሚመች ሰፊ ግቢ አለን።
15.ከአዲስ አባባ (ፊንፊኔ) በስተምስራቅ የቅርብ ርቀት (40 ደቂቃ የመኪና ጉዞ) በምትገኘው የታላቁ ስምጥ ሸለቆ ዕንቁ በሆነችው አዳማ ከተማ እንገኛለን።

በመሆኑም የራሳችሁን የት/ት ስርዓት በመቅረፅ በአጭር ጊዜ ከፍተኛ ሳይንቲስትና ቴክኖሎጂስት በመሆን የሀገራችን ብሎም የአፍሪካ ህዳሴ አካል እንዲትሆኑ **አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲን ምረጡ!**

አደማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ፣ አዳማ፤ ኢትዮጵያ